# ስለ "ሰላማዊ የስልጣን ሽሽግግር" እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች: አጭር ቅኝት

ገብረ ሥላሴ አርአያ

26 መጋቢት 2010 ዓ/ም

የቀድሞ ጠ/ሚ ሃይለማሪያም ደስለኝን ከስልጣን መልቀቃቸውን ተከትሎ በአራቱ የኢህአዴግ ድርጅቶች አማካኝነት ወደ ስልጣን የመጡት ዶ/ር አብይ አህመድ አስመልክቶ በሁሉም ሚዲያዎች (በመንግስትና፣ በግልና እና የኤርትራ መንግስት ፋይናንስ በሚያደርገው ESAT ቴሌቪዥን ሳይቀር) ስለ ስልጣን ሽግግር እየተወራ ስንብቷል አሁንም ቀጥለዋል። አንዳንዶቹ ሚዲያዎችም "ካለ ምንም ደም አፋሽነት የስልጣን ሽግግር" እንደተካሄደ አፋቸውን ሞልተው ትንታኔ ለመስጠት ሞክረዋል። ለምሳሌ አበበ ባዩ በENN። ሚዲያዎች ብቻም አይደሉም። አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናትም ጭምር ይሄንን አባባል እየተጠቀሙበት ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ሳያውቀው ሚዲያውች ብቻ ያወቁት ነገር ይኖር ይሆን ብየ ሰሞኑን ብጠብቅም አዲስ ነገር አልተገኘው እሱን መደጋገም ሆነ።

እንግዲያውስ የስልጣን ሽግግር የሚባለው የተለያየ አላማ እና የፖለቲካ መርሃ ግብር ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ፉክክር አድርገው በስልጣን ላይ የነበረው አካል ለተፎካካሪው ስልጣኑን ሲለቅና ሙሉ በሙሉ የመንግስት ለውጥ ሲኖር ብቻ ነው። ለምሳሌ ከዴሞክራቱ ባራክ አባማ መንግስት ወደ ሪፓብሊካኑ ዶናልድ ትራምፕ መንግስት ሰላማዊ የሆነ የስልጣን ሽግግር አድርገዋል። እስከሚገባኝ ድረስ በአገራችን እንዲህ አይነት ነገር አልተፈጸመም። በኢትዮጵያ ሁኔታ የተፈጸመው የስልጣን ሽግግር ሳይሆን ኢህአዴግ ሊቀመንበሩን በመቀየር የጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታው የሚያስቀጥሉለት ሰው ነው የመረጠው። አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስተር ይዘውት የሚመጡ አዲስ ነገር ኣለ ከተባለም ድርጅታቸው ኢህአዴግ በአመራር ድክመት ምክንያት ማስፈጸም ያቃተውን የህግ የበላይነት፣ ተጠያቂነት፣ መልካም አስተዳደር፣ ሰላም፣ ልማት እና ሌሎች ጉዳዮች የተሻለ የአመራር ብቃት በማሳየት ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው መስራት ይሆናል። በሁሉም ህዝቦች ዘንድ እየተጠበቀ ያለውም ከዚህ የተለየ አይደልም። የሚገርመው ግን ይህ "ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር" ተደረገ የሚለውን አባባል በየቀኑ በመንግስት ሚዲያዎችም ጭምር እየተጠቀሙበት ባለበት ሁኔታ አንድም የኢህአዴግ ሰው ወይም ጽህፈትቤቱ እርማት ሊሰጥ ያለመሞከሩ ነው። አባባሉን ተመችቶት ይሆን?! ያስብላል።

ሌላው በጸረ ኢህአዴግነታቸው የሚታወቁ ጽንፈኛ ተቃዋሚዎች፣ በተለይም ህወሀት እና የድርጅቱ ማህበራዊ መሰረት የሆነውን የትግራይን ህዝብ እስከ የዘር ማጥፋት እርምጃ እንዲወሰድበት ያወጁ በESAT እና በእሱ ዙሪያ የተሰባሰቡ ሃይሎችም ሳይቀር የአዲሱን ጠቅላይ ሚኒስተር ደጋፊ ወደ መሆን መሸጋገራቸው ነው። እሰየው እንኳን ለዚህ አበቃቸው። ጉዳዩ ግን ግልጽ ነው። እነዚህ ሃይሎች የፈለጉት አዲሱን መንግስት ጠልፈው ጉዳያቸው አስፈፃሚ የማድረግ ምኞት ስላላቸው እንደሆነ ለማንም ግልፅ ነው። እንዲያው አዲሱ ጠ/ሚ ገና ቢሮ ከመግባታቸው ጀምሮ እንትናን አውርደህ እንትናን ስቀል የሚሉ መመሪያዎች ለመስጠትም እየሞከሩ ይገኛሉ። ይህ ይሳካ ይሆን? ኢህአዴግም ይሁን ማነኛውም መንግስት የሚመሰርት የፖለቲካ ድርጅት ጉዳዩን (የፖለቲካ ፕሮግራሙና ፖሊሲው) የማያሳፈጽምለት ሊቀመንበርም ይሁን ጠቅላይ ሚኒስተር ይዞ መቀጠል እንዳማይችል ለማንም ግልጽ መሆን ነበረበት። በአጭሩ አዲሱ ጠ/ሚ ቦታው የተሰጣቸው የኢህአዴግን ፕሮግራም ለማስፈጸም ነው። እሳቸውም ከዚህ የተለየ አላማ ያላቸው ሰው አይደሉም። ከዚህ ጋር ተያይዞ በምን መልኩ እንደሆነ ባይዘረዝሩትም በዶክተር አብይ የሚመራውን ኢህአዴግ ከተቃዋሚዎች ሳይቀር ድጋፍ ማግኘቱ በአገሪቱ እየተካሄደ ያለውን የማልቲ ፓርቲ ሂደት እንደሚጎዳው የኢዴፓው ልደቱ አያሌው ይገልፃሉ። ለተቃዋሚዎችም ልክ ኢህአዴግ እንዳደረገው ጥልቅ ግምገማ እንዲያደርጉ ይመክራሉ።

በመጨረሻ አንድ የሚገርመኝ ነገር ላንሳ እና ልሰናበት። የኢህአዴግን ዝግ ስብሰባና በሚስጥር የተካሄደው የሊቀመንበር ምርጫ እንትና ፓርቲ ለዶ/ር አብይ ተቃወመ እንትና ግን መረጠው የሚሉ ሽልኮ የደረሰን መረጃ አለ የሚሉ መብዛታቸው ነው። ይህ

ኣሉባልታ ተከትሎ ድግሞ ብዙ ሰዎች በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ወሬውን እንደ እውነት በመውሰድ ትንተና ሲሰጡ ሰንብተዋል። ለዚህ ኣሉባልታ እና ግራ መጋባት ትልቅ ኣስተዋፆ ያደርጉት ሁለት ሁኔታዎችን ልጥቀስ። ኣንደኛው፣ ልክ ምርጫው እንዳለቀ በብኣዴኑ የኮሚኒኬሽን ሃላፊው ንጉሱ ጥላሁን በፌስቡክ የለጠፉት ኣስተያየት እና የብኣዴን ሊቀመንበሩ ደመቀ መኮንን ቆየት በለው የሰጡዋቸው ኣስተያየቶች የዶ/ር ኣብይን መመረጥ የድርጅታቸው እጅ እንዳለበት የሚጠቁሙ መልእክቶች ማስተላለፋቸው ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ በጥቆማው ሂደት ነበረ የተባለው ጠንከር ያለ ክርክር ነው። ጠንከር ያለ ክርክር ማድረጉ እና ኣብሮ መቀጠሉ ለኢህኣዴግ ኣዲስ ነገር ባይሆንም ብኣዴኖች እንዲህ ኣይነት መልእክት ማስተላለፍ ያስፈለጋቸው ምክንያት ምንድ ነው ብሎ ማስቡና ጉዳዩ በጥልቀት መመርመሩ ተገቢ ነው ብየ ኣምናለሁ። በኮሚኪኬሽን ሃላፊውና በኣቶ ደመቀ ሞኮነን የተሰጡ ኣስተያየቶች እንዲሁ የኣጋጣሚ ጉዳይ ሳይሆን ሆን ተብሎ ታስቦበት የተደረገ ቀናነት የጎደለው ኣካሄድ ነው። ***ለመሆኑ ብኣዴኖች ዶ/ር ኣብይን መርጠው ይሆን???*** በበኩሌ ኣይመስለኝም። ምርጫው በሚስጥር ስለተካሄደ ግን ማን ለማን እንደመረጠ የሚያውቅ ኢህኣዴግም ሆነ ግለሰብ እንደሌለ መገንዘብ ኣስፈላጊ ነው።

ቸር ይግጠመን